# ከምርጫ ጋር ተያይዞ ለሚፈፀሙት ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የወጣ ሕግ ከ1996 አዲሱ የወንጀል ሕግ የተወሰደ የሕግ ድንጋጌዎች

## የወንጀል ሕግ

## ርዕስ አምስት

## በሕዝባዊ ምርጫዎችና በድምፅ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

### አንቀጽ 466 ለምርጫ የሚደረግ ስብሰባንና የምርጫ ሂደትን ማወክና ማሰናከል

1. ማንም ሰው በሕግ የተፈቀደ ከምርጫ ጋር የተገናኘ ሕዝባዊ ስብሰባን ወይም በሚመለከታቸው ባለሥልጣኖች ቁጥጥር በአግባቡ የሚደረግ የድምፅ አሰጣጥን ወይም ምርጫን አግባብ በሌለው በማናቸውም መንገድ ያወከ፣ የከለከለ፣ ያደናቀፈ ወይም እንዲቋረጥ ያደረገ አንደሆነ@

   ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራትና ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በሰዎች ወይም በንብረት ላይ የኃይል ድርጊት ተፈጽሞ እንደሆነ@ ወይም የአምባጓሮ ወይም የሁከት ጠባይ ያለው ረብሻ ተነስቶ እንደሆነ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በተ ደራቢነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

### አንቀጽ 467 የምርጫ ድምፅ የመስጠትን ወይም የመመረጥን መብት መንካት

1. ማንም ሰው በዛቻ፣ በማስገደድ፣ በሥልጣኑ ያለአግባብ በመጠቀም ወይም በኃይል ድርጊት፣ በማጭበርበር በተለይም ስምን በመለዋወጥ፣ ማስታወቂያን ወይም መጥሪያን በመደበቅ ወይም በማስቀረት ወይም በማናቸውም ሌላ ብልሀት ወይም ዘዴ፡-
   ሀ/ ሌላ ሰው በመምረጥ ወይም በመመረጥ መብቱ እንዳይጠቀምበት የከለከለ አንደሆነ@ ወይም
   ለ/ ይህን በመሰለ ዘዴ ሌላ ሰው መብቱን በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም በዚሁ መብቱ ሳይጠቀምበት ለመቅረት ግዴታ እንዲገባ ያደረገ ወይም ያግባባ እንደሆነ@

   ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንም ሰው እንደፍላጎቱ ለመጠቀም በተሰጠው መብት መሠረት የመምረጥ መብቱን

በአንድ በተወሰነ መንገድ በተጠቀመበት ወይም ሳይጠቀምበት በቀረው ሰው ላይ በደል ወይም ጉዳት ያደረሰበት እንደሆነ@

ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ 468 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ*

1. ማንም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለውን ሌላውን ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እንዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ፣ ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ@

   ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራትና በመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ማንም ሰው በዚሁ መብቱ እንዲጠቀምበት፣ ወይም በአንድ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀምበት ወይም ሳይጠቀምበት እንዲቀር ገንዘብ ወይም ማናቸውንም ሌላ ዓይነት ጥቅም የተቀበለ ወይም ለመቀበል የተስማማ እንደሆነ@ ከዚህ በላይ በተመለከተው ቅጣት ይቀጣል፡፡

## *አንቀጽ 469 የማይገባ አሠራር*

1. ማንኛውም እጩ ተመራጭ በሕግ ከተፈቀደው ውጭ ለምርጫ ዘመቻ ወጪ የሚሆን ገንዘብ ከማናቸውም ሰው፣ ቡድን ወይም ድርጅት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሰበሰበ ወይም የተቀበለ እንደሆነ@ ወይም የተወሰነውን የምርጫ ውድድር ሂሣብ ማቋቋሚያ ደንቦች ያላከበረ እንደሆነ ወይም በምርጫ ውድድር ሂሣብ ውስጥ ወጪውን አስቦ አሳንሶ ያመለከተ አንደሆነ@

   ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንም ሰው ከእጩ ተመራጩ ፈቃድ ሳያገኝ የአንድን እጩ ተመራጭ የምርጫ ወጪ ለመሸፈን ገንዘብ ያሰባሰበ፣ የሰጠ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ አስተዋጽኦ ያደረገ እንደሆነ@

   ከላይ የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል፡፡

3. ማንም ሰው በቀጥታ ወይም በሌላ ሰው አማካይነት፡-
   ሀ. በሰው በማስነገር፣ በመጻጻፍ፣ በፖምፍሌት፣ በሚለጠፍ ጽሁፍ ወይም ስዕል፣ ታትሞ በሚወጣ ጽሑፍ፣ በራዲዮ ወይም በማናቸውም ሌላ የሕዝብ መገናኛ ዘዴ በሚሰራጭ ሐሰተኛ ዜና ወይም ወሬ በመታገዝ @ወይም

3.

ለ/ በማናቸውም ሌላ የማጭበርበር፣ የማዛባት ወይም ከሐቀኛ አሠራር ውጭ በሆነ

መንገድ በመታገዝ@

አጭበርብሮ የመራጭ ድምጽን ያገኘ ወይም በመራጭ ድምጽ ያለአግባብ የተገለገለ ወይም ድምፁ መራጩ ለመረጠው ሰው እንዳያገለግል ያደረገ

እንደሆነ@

ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአምስት ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

***አንቀጽ 470 በአመዘጋገብ ላይ የሚፈጸም ማጭበርበር***

1. ማንም ሰው፡-
   - ሀ/ በምርጫ ዝርዝር ወይም በምርጫ መዝገብ ውስጥ በሐሰተኛ ስም ወይም ማዕረግ ወይም በሌለው ችሎታ እንዲመዘገብ ያደረገ ወይም ያለበትን በሕግ የታወቀ ችሎታ ማጣት ሳይገልጽ የተመዘገበ እንደሆነ@
   - ለ/ በአንድ ጊዜ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ የምርጫ ዝርዝሮች ወይም መዛግ ብት ስሙን ያስመዘገበ ወይም ያለአግባብ ብዙ የድምጽ መስጫ ወይም የምርጫ ወረቀቶችን የተቀበለ ወይም እንዲሰጡት ያደረገ እንደሆነ@ ወይም
   - ሐ/ ያለአግባብ በሕይወት ያሉ፣ የሞቱ፣ የጠፉ፣ ወይም በሕይወት ኖረው የማያውቁ ሰዎችን ያስመዘገበ ወይም በእነርሱ ስም የድምጽ መስጫ ወረቀቶች የተቀበለ እንደሆነ@

   ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ወንጀል በእጩ ተመራጭ በተፈጸመ ጊዜ ቅጣቱ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጽኑ እሥራት ወይም ከአሥር ሺህ ብር ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል፡፡

**<u>አንቀጽ 471 በድምጽ አሰጣጥ ጊዜ የሚፈጸም የማጭበርበር ድርጊት</u>**

ማንም ሰው ማናቸውም ዓይነት የታወቀ ምርጫ በሚደረግበት ጊዜ፣ከምርጫው በፊት፣ በምርጫው ጊዜ፣ወይም ከምርጫው በኋላ በሚፈጸም በማናቸውም ዓይነት ድርጊት በተ ለይም፡-

ሀ/ የምርጫ መዝገብን፣ የተጠናቀቀ የምርጫ ዝርዝርን፣ወይም ድምፅ የተሰጠበትን የድ ምፅ መስጫ ወረቀትን አስመስሎ በመሥራት፣ ሐሰተኛ በማድረግ፣ በመለወጥ፣

በሚያሳስት ዘዴ በላዩ ላይ በማተም፣ወይም በማስቀረት፣በማጥፋት ወይም በመውሰድ@



ለ/ በአንድ የምርጫ ጊዜ ከአንድ ጊዜ በላይ ድምጽ በመስጠት@

ሐ/ የድምፅ መስጫ ወረቀትን በድምፅ መስጫ ሣጥን ውስጥ በመጨመር ወይም ከምርጫ ሣጥን አውጥቶ በመውሰድ፣ ወይም በማናቸውም መንገድ ያለአግባብ ሕጋዊ መኖሪያ ቦታው ምርጫ ከሚደረግበት አካባቢ ውጭ የሆነውን፣ ችሎታ የሌለውን፣ ችሎታ ያጣውን ሰው ድምፅ እንዲሰጥ፣ ወይም በሞተ ወይም ሕይወት ኖሮት በማያውቅ ሰው ስም ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ወይም ለድምፅ መስጫ እንዳያገለግል የተደረገ፣ ወደ ሐሰተኛነት የተለወጠ፣ ወይም በሀሰት የተሠራ የድምፅ መስጫ ወረቀትን እያወቀ በምርጫ ሣጥን ውስጥ በማስገባት ወይም እንዲገባ በመፍ ቀድ@ ወይም

መ/ የድምፅ መስጫ ወረቀትን በትክክል ባለመቁጠር ወይም ታስቦ የተሰጠ ድምፅን፣ ድምፅ የተሰጠበትን ወረቀት፣ ስምን ወይም ፊርማን በመተው፣ ወይም ከተጻፈው ፊርማ ወይም ስም ሌላ በማንበብ ወይም በምርጫው ሥነ ሥርዓት ቃለ ጉባዔ ወይም በኦፊሴላዊ የምርጫ ውጤት ላይ ከእውነተኛው ነገር ውጭ በመመዝገብ@ ወይም

ሠ/ የምርጫ ውጤትን ወይም ሰነድን በማስቀረት፣ በመደበቅ፣ በመለዋወጥ ወይም በማ ጥፋት ወይም እነዚህን ለመቀበል ሥልጣን ለሌላቸው ሰዎች ያለአግባብ በመስጠት፣ የምርጫውን ትክክለኛ ውጤት ያሳሳተ አንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

***<u>አንቀጽ 472 የወንጀሎች መደራረብ</u>***

የተፈፀመው የማጭበርበር ወይም ወደ ሐሰት የመለወጥ ወንጀል የተሠራው በግዙፍ ወይም በረቀቀ ዘዴ እንደሆነ፣ ይህንኑ ጉዳይ የሚመለከተው የቅጣት አወሳሰን ድንጋጌ በተደራቢነት ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ 365፣ 366/፡፡

***<u>አንቀጽ 473 የድምፅ አሰጣጥ ምስጢር አጠባበቅን መጣስ</u>***

ማንም ሰው፡-

ሀ/ አንድ መራጭ ያለውን መብቱን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደተገለገለበት ወይም ድምፁን እንደሰጠ ሕገወጥ በሆነ መንገድ ለማወቅ የቻለ እንደሆነ@ ወይም

ለ/ የዚህን ዓይነት ጉዳይ በአጋጣሚ ካወቀ በኋላ በቃልም ሆነ በጋዜጣ ወይም በሌላ ዓይነት ዘዴ አስቦ ለሕዝብ የገለጸ ወይም ወሬውን የነዛ እንደሆነ@

በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

5.

## *አንቀጽ 474 የድምፅ መስጫ ወረቀቶችንና የምርጫ ሣጥኖችን መውሰድና ማጥፋት*

1. ማንም ሰው ድምፅ ተሰጥቶባቸው ያልተቆጠሩ የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን የያዘ የምርጫ ሣጥንን ወይም በሣጥኑ ውስጥ የሚገኙትን የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በሙሉ ወይም በከፊል ከቦታው ያነሣ፣ እንዲሰውሩ ያደረገ ወይም የጠፋ እንደሆነ@

   በቀላል እሥራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ወንጀሉ የተፈፀመው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች ወይም በኃይል ድርጊት እንደሆነ ለአለቆቹ ወይም ለመሪዎቹ ስለ ቅጣት ማክበድ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ/አንቀጽ 84(መ) ቅጣቱ ከአሥር ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይሆናል፡፡
3. በምርጫ ጣቢያ ላይ ወይም በምርጫ ጣቢያ አባሎች ላይ የሚፈፀም የኃይል ወይም የማስገደድ ድርጊት በዚህ ሕግ ከአንቀጽ 440 እስከ 442 በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል፡፡

# ከምርጫ ጋር ተያይዞ ለሚፈጸሙት ወንጀሎች ጋር በተያያዘ የወጣ ሕግ ከ1996 አዲስ የወንጀል ሕግ የተወሰደ የሕግ ድንጋጌዎች